# በላብ አደር ካባ በታኘ ወያኔያዊ ደባ

## አቶ ዳዊ ኢብራሂም በቅርቡ በኢንተርኔት ላሰራጨው አሉባልታ በስደት ከምንገኝ የኢትዮጵያ ሰራተኛ ማሕበራት መሪዎች የተሰጠ ምላሽ

በቅርቡ ኢትዮጵያን ሪቭው ድረ ገጽ ላይ አቶ ዳዊ ኢብራሂም ያወጣውን ጽሑፍ አንብበነዋል። በዚህ ጽሑፉ ያስነበበን በቁጣ ፤ በንዴት እና በድንጋጤ የተጻፈው ድርሰቱ ደግሞ ስደተኛ የማሕበር መሪዎች በቅርቡ በአዲስ መልክ ለመሰባሰብ እና ጸረ ወያኔውን ትግል ለማገዝ እያደርግን ያለነው ጥረት ላይ የተመረኮዘ ነው።

አቶ ዳዊ ኢብራሂም በሰራተኛ ማሕበር መሪነት ስም እንደመሰደዱ ሊያስታውሰው እና ሊዘክረው ይገባው የነበረውን ይህን ዓቢይ ቀን ነገር ግን ቁም ነገር ብሎ ያላስታወሰውን የዘንድሮውን ዓለም አቀፍ የሰራተኞች ቀን ሜይ ዴይን የአሲምባ የፓልቶክ ፎረም አስታውሶ ለመዘከር ባቀናበረው ዝግጅት ከ1960ዎቹ እስከ አሁን በኢትየጵያ ሰራተኞች ትግል የተሳተፉ የማሕበር መሪዎችን ጋብዞ በግልጽ እና በአደባባይ ሕዝብ እየሰማ አነጋግሮአል።

በዝግጅቱ ወቅት በወያኔ አገዛዝ ዘመን በኢትዮጵያ ሰራተኛ ማሕበራት ኮንፌዴሬሽን (ኢሰማኮ) ላይ አገዛዙ ባወረደው አረመኔአዊ በትር ለስደት ከተዳረጉት የኮንፌዴሬሽኑ አመራር አባላት መሃከልም ሶስት አባላት ተሳትፈው ነበር። በውይይቱም እነዚህ አባላት ወያኔ እና አገዛዙ በማሕበራቸው ላይ ያደረሰውን በደል ተንትነው ግፉን ኢጋልጠዋል። አውግዘዋል። የሰራተኛው መብት እስኪከበር እንደሚታገሉም አስረግጠው ተናግረዋል።

ይህ ውግዘት እና ቁርጠኝነት አቶ ዳዊን አስደንግጦታል፤ አበሳጭቶታልም።

የአሲምባ ፓልቶክ ታዳሚዎች እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ የኢትዮጵያ ሰራተኛ ማሕበር መሪዎችን ለመተቸት ያላቸዉን ዴሞክራሲያዊ መብት ተጠቅመው በስደት የምንገኝ የኢሰማኮ መሪዎችን ተችተዋል። እስካሁን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወያኔ ጋር ጉሮሮ ለጉሮሮ ተናንቆ ሲዋደቅ እናንተ በሰራተኛው ስም ተሰዳችሁ ድምጻችሁ አይሰማም፤ መኖራችሁም አይታወቅም፤ ስለ ሰራተኛ ማሕበር እንቅስቃሴም ምንም አይሰማም ለመሆኑ ምን ሆናችሁ ነው ድምጻችሁ የጠፋ የሚል ወቀሳና ጥያቄ አቅርበዋል። ተገቢ ወቀሳም ነበር። የዝምታችንን ምክንያት ያላወቁ ሁሉ እንደ አሲምባ ፓልቶክ ተሳታፊዎች በተገኘው መድረክ ሁሉ ሲወቅሰን ኖሮአል።

ለምን መሰብሰብ እንዳልቻልን፤ ተሰባስበን ጸረ ወያኔ ትግሉን እናግዝ ባልን ቁጥር ማን እንደሚዘምትብን እና ጸረ ወያኔ ጥረታችንን እንደሚያደናቅፍ፤ በችግር ለሚቆላው እና በአገዛዙ ለታፈነው ሰራተኛ ድምጽ እንሁን ስንል ማን ጎሮሮአችንን እንደሚያንቀን ፤ ማን እራሱን በልክስክስ የስነ ምግባር ጉድለት እና ጸያፍ ተግባራት አሰማርቶ አንገት እንዳስደፋን፤ ለሕዝብ መንገር ; ሕዝባችንን በአጠቃላይ እና በተለይም የመረጠንን ሰራተኛ አንገት ማስደፋት፤ ለወያኔ የፕሮፓጋንዳ ወፍጮም ግራሶ ማቀበል ነው ብለን ፤ በጸረ ወያኔ ትግሉ ላይ የሚያሳድረውንም አሉታዊ ተጽእኖም ከግምት በማስገባት ተናግረን ሕዝባችንን ተስፋ ከምናስቆርጥ እና ሰራተኛውን እና የሰራተኛውን ቤተሰቦች አንገት ከምናስደፋ እንዲሁ አሉ እየተባለ ተሸፋፍኖ ቢቀጥል ይሻላል ብለን ሆዳችንን እያመመን አምቀነው ኖረናል። በውይይቱ ወቅት ችግራችንን እንድናስረዳ ጥያቄ ቢቀርብልንም የውስጥ ችግራችንን በመድረክ እንደማናቀርበው ፤ በጥቅሉ ግን ለመሰባሰብ የተደረጉ እልህ አስጨራሽ ፤ አንጀት በጣሽ ጥረቶች እንደነበሩ አውስተን አሁንም ቢሆን ተስፋ ሳንቆርጥ ለመሰባሰብ ጥረት እንደምናደርግ አስረድተናል።

በዕለቱ በአሲምባ ፓልቶክ የተደረገውን ውይይት አሲምባ ድረ ገጽ http://www.assimba.org/ ላይ ሙሉው ቅጅ ስለሚገኝ አዳምጣችሁ እዚህ ካልነው ውጭ የተባለ ካለ ማንም የሰራተኛ ወገን እና ኢትዮጵያውያን ሁሉ ሊተቹበት ይችላሉ።

ተሰባስበን ጸረ ወያኔ ትግሉን እናግዛለን ባልነው መሰረትም እነሆ አዲስ የማሰባሰብ ጥረት እያደረግን ነው። በስደት የምንገኝ የቀድሞ የኢትዮጵያ ሰራተኛ ማህበር መሪዎች ሰብሳቢ አጥተን፤ መሪ ከድቶን፤ ተበ ታትነን ዓመታት አስቆጥረናል ። እነሆ አሁን ከተበተንበት እንደገና ለመሰባሰብ የጀመርነው ጥረትም አቶ ዳዊ ኢብራሂምን አስደንግጦታል። በድንጋጤ ተነሳስቶም ውግዝት እና እርግማኑን በኢትዮጵያን ሪቭው ድረ ገጽ ላይ አውርዶብናል ።

በእኛ በኩል ግን አቶ ዳዊን ጨምሮ አድራሻቸውን ላገኘነው የቀድሞ ማሕበር መሪዎች በሙሉ ኑ እንሰባሰብ፤ ኑ እንመካከር ፤ ኑ ጸረ ወያኔውን ትግል እናግዝ ብለን ጥሪያችንን አቅርበናል። የውይይት መድረካችንን መኖርም አሳውቀናል። ጥሪያችንን አክብረው ከተገኙት ጋርም ውይይት ጀምረናል።

በኢሰማኮ ውሳኔ ከተባረሩት ከተወገዱት እና ከወያኔ ጎን ቆመው ሰራተኛውን ከወጉት ከሃዲዎች በስተቀር ስደተኛ የማሕበር መሪዎች አቶ ዳዊን ጨምሮ ፤ ሁሉንም አካቶ ማንንም ወደ ውጭ ሳይገፋና ሳያገል በሚያሰባስብ መድረክ ተሰባስበው ጸረ ወያኔውን ትግል ማገዛቸው ምን ክፋት ኖሮት ነው በአቶ ዳዊ የተዘመተበት?

ስርዓት ያለን ነን እና እንቅስቃሴአችን በተጻፈ ሕግና ደንብ መመራት እንዳለበት በማመን ለመተደዳሪያ ደንብ ዝግጅት ቅድሚያ ሰጥተን ረቂቅ ሕገ ደንብ ማዘጋጀት ጀምረናል። በግለሰባዊ አምባ ገነንነት ስር ተጠፍረን የደረስንብንን ውድቀት አልረሳንምና ሊጋራ አመራር ቅድሚያ ሰጥተን ሁሉም እኩል የሚጉዋዝበት መድረክ እንዲሆን ተስማምተን የጋራ ጉዞ ጀምረናል። ግልጽነትን መርሃችን በማድረጋችን ይህን ሁሉ እንቅስቃሴ ለአቶ ዳዊ ጭምር አሳውቀናል። ትኩረት ለትግሉ ሰጥተን እና የአቶ ዳዊን ገበና ሽፍነን ለመቀጠል ተስማምተን በመድረካችን እንዲሳተፍም ጋብዘነዋል። ከአቶ ዳዊ ያገኘነው መልስ በኢትዮጵያን ሪቭው ላይ የጻፈው ልብ ወለድ ድርሰት ነው። እኛው እራሳችን የነገርነውን ጉዳይ ታላቅ ሴራ ሲጠነሰስ ደረስኩበት ሲልም ቀድሞውኑ በግልጽ የነገርነውን ግልጽ እንቅስቃሴ አጋላጭ ሆኖ በራሱ ድርሰት ውስጥ ለራሱ የጅግና ገጸ ባሕሪ ሰጥቶ ጀግናም ሲባል እየታያው የተለመደውን የአሉባልታ ዘመቻ ከፍቶብናል።

መተዳደሪያ ደንባችንን ከማርቀቁ ጎን ለጎን ልንሰራቸው ይገባል ብለን ከተወያየንባቸው ነጥቦች መሃከል ከኛ ጋር በትግሉ ተሳትፈው በወያኔ የቂም በቀል እርምጃ ከስራ የተባረሩና እስከ ዛሬ አስታዋሽ ያጡትን ወንድሞቻችንን መርዳት፤ በስደት እየተንከራተቱ ያሉትን የነጻው ፕሬስ አባላት መርዳት ወዘተ የሚል ነበር። የጅማሮአችን አቅጣጫም በስደት ከሚገኙ የሲቭክ ማሕበረሰቡ ቤተሰቦች ጋር ተሰባስበን የጋራ መድረክ በመፍጠር ጸረ ወያኔውን ትግል በተቀናጀና ሁለ ገብ በሆነ መልክ ማገዝ ነው። አቶ ዳዊ እነዚህን መልካም ሃሳቦቻችንን እና ትልማችንን በሚገባ እያወቀ ስለነዚህ እርምጃዎቻችን ምንም ሳይል እንዳልሰማና እንዳላወቀ ሆኖ ይህን አዲስ የመሰባሰብ ጥረት ለመበታተን ይረዱኛል ያላቸውን ሃረጎችና ሃሳቦች ገና በፍሬ ነገር ውይይት ካልተደረገበትና ሃሳብ በማሰባሰብ ደርጃ ካለው ድራፍት ሕገ ደንባችን እየጠቀሰ ለድርሰቱ ማዳበሪያ ማዋሉ እቅዱ ጥረታችንን ከማፍረስ እና ከማደናቀፍ ጋር ብቻ የተያያዘ ለመሆኑ ማስረጃ ነው።

ከስራ የተባረሩና እስከ ዛሬ አስታዋሽ ያጡትን ወንድሞቻችንን ለመርዳት ማሰባችንን የሰማው አቶ ዳዊ በስማቸው ዶላር ሲያፍስባቸው የኖሩትን እና ለዘመናት ያላስታወሳቸውን ሰዎች በአንድ ተላላኪው አማካይነት አዲስ አበባ አስደውሎ የተቸገሩ የማሕበር መሪዎችን ልረዳ ስለሆነ የት ነው ያሉት ማለት መጀመሩን ሰምተናል። ይህ ደግሞ ቅን ከሆነ ዓላማ ሳይሆን የኛን ጥረት ለማደናቀፍ ይረዳኛል በሚል ዕኩይ አስተሳሰብ ላይ የተመሰረተ እንደሆነ እናውቃለን።

አቶ ዳዊ ኢሕአፓ ያሳደገኝ አባቴ ነው ሲል እንዳልኖረ አሁን አባቴ ሲለው የኖረውን ኢሕ አፓን ለማውገዝ በጻፈው በዚህ ድርሰቱ እኛ ስደተኛ የሰራተኛ ማሕበር መሪዎች በአዲስ መልክ ለመሰባሰብ የምናደርገውን ጥረት በያንዳንዱ ፓራግራፍ መሃል እንድ አዝማች አድርጎ በማስገባት እጅ እጅ ለሚለው የሃሰት ድርሰቱ ወዝ ሊሰጠው ሞክሮዋል፡; አቶ ዳዊ ብረት አንግቦ ኢሕአፓን ሲያገለግል በነበረበት ዘመን እሱና "አባት ድርጅቱ" ለሰሩት ተግባር በወቅቱ ከታዳጊ ያለፈ እድሜ ያልነበራቸውን ሰዎች ስም እየጠሩ ለማነካካት የተደረገውም አይን ያወጣ ማጭበርበር አቶ ዳዊን ትዝብት ላይ ከመጣል ያለፈ ፋይዳ የለውም።

አቶ ዳዊ እና አባት ድርጅቱ ኢሕአፓ እንደ አባትና ልጅነታቸው ቢሻቸው በመድረክ ቢሻቸው በር ዘግተው ያገባናል በሚሉት ጉዳይ ላይ ሁሉ ሊወያዩ ይችላሉ። ስደተኛ የሰራተኛ ማሕበር መሪዎች የጀመርነውን የመሰባሰብ እንቅስቃሴ ግን ከየትኛውም የፖለቲካ ድርጅት ጋር ማነካከት አንፈቅድም።

አቶ ዳዊ በተደጋግሚ እንደ ሱፍ አበባ ጸሃይ በታየበትና በሞቀብት ሁሉ ያለ ይሉኝታ እየተሽከረከረ ሲጣድ የኖረ ናውና ዛሬም ወደሞቀበት ፊቱን አዙሮ አዲሱን ጸሐይ ለመሞቅ ይችላል የምስኪን ስደተኛ ሰራተኛ መሪዎችን ቅን የመሰባሰብ እና ጸረ ወያኔ ትግሉን የማገዝ ጥረት ግን ጭዳ ማድረግና በእጅ መንሻነት ማቅረብ አንፈቅድለትም።

አቶ ዳዊ በደረሰው ባለ 6 ገጽ ድርሰት በየፓራግራፉ ስማችንን እንደ ግጥም አዝማች ደጋግሞ ቢያነሳም እኛን የሚመለከከት ወይም እኛን ኢሕአፓ ሰራ ከሚሉት "ወንጀል" ጋር የሚያነካካበት አንድም ነጥብ ማቅረብ አልቻለም። ሌላው ቀርቶ እኛ በተሳተፍንበት የኢሰማኮ እንቅስቃሴ ውስጥ እንኩዋን ኢ ሕ አ ፓ ይህን ሰራ የሚለው አንዲት "ወንጀል" ማቅረብ አቅቶታል። ለመጀመሪያ ጊዜ የኢሕአፓና የኢሰማኮ ታሪክ የተነካኩትም በራሱ በዳዊ የስደት አወጣጥ ሂደትና በስደት ቆይታው ወቅት እንደሆነ በድርሰቱ ገጽ 4 ላይ አረጋግጦልናል። የእሱ የስደት አወጣጥ እና በናይሮቢ ቆይታው ወቅት ኢሕአፓ ያደረገለት እንክብካቤ ወዘተ ናቸው የኢሰማኮና ኢሕአፓ ንክኪ የመጀመሪያ አሻራዎች።

አቶ ዳዊ ወያኔ ያዋቀረው የኢትዮጵያ ሰራተኛ ማሕበራት አደራጅ ኮሚሽን ሆኖ ባገለገለበት ዘመን ከወያኔ ካድሬዎች ቀጥተኛ አመራር እየተቀበለ ለ 6 ወራት የገመደውን የብረት ሰንሰለት ቆራጦቹ የኢትዮጵያ ላብ አደር መሪዎች በጥቂት ቀናት ትግል ብትንትኑን አውጥተው አቶ ዳዊን ጭምር በምርኮኝነት አንበርክከው ማሕበራቸውን በነጻነት መመስረታቸው አቶ ዳዊን እስከዛሬም እንደሚቆጨው ያለ ሐፍረት ገልጾዋል። የኢትዮጵያ ላብ አደሮች በኢሰማኮ ምስረታ ወቅት ያሳዩትን ወደር የለሽ ጸረ ወያኔ ትንቅንቅ እና የገኙትንም ድል አቶ ዳዊ ሲገልጸው "የኢትዮጵያ ሰራተኞች እንደገና ሲደራጁ ኢሕአፓ በሰራተኛው እንቅስቃሴ ውስጥ አንድ አማሽ ሰርጎ ገብ አስርጋ በማስገባት ችግር ለመፍጠር ጥረት አድርጋለች" ይላል። ታሪክን እንዲህ እየበረዘ ወደየት መጢጋት እንደፈለገም አይምሮ ላለው ሁሉ ግልጽ ነው።

አቶ ዳዊ በደረሰው ባለ 6 ገጽ ድርሰት ኢሕአፓ ሰራ ያላችዉን "ወንጀሎች" በሙሉ ሲሰራ እራሱም የኢሕአፓ አባል ነበረና ቢያንስ እስከነበረበት ጊዜ የተፈጸመው ድርጊት ተዋናይነቱን ወደኛ ለማቀበል መሞከሩ ጭንቀት የወለደው አጉል መላ ከመሆን አያልፍም።

ትላንት በኢሰማኮ ጽ/ቤት ተቀምጦም ሆነ በስደት አምስተርዳም ላይ ሆኖ ባንዳና ከሃዲ እያለ በመግለጫዎቹ ላይ ሁሉ ሲያወግዛቸው ለነበሩት ለእነ ጣምያለው እሸቴ ዛሬ የአዞ እንባ አፍሳሽ ሆኖ መቅረቡም የጤና ነው አንልም። አላወገዝኩአቸውም ከሃዲ ባንዳና ሆዳም አላልኩዋቸውም ካለ በታይፕ ሳይሆን በራሱ የጅ ጽሑፍ ቁልጭ ብሎ የተጻፈ ማስረጃ ማቅረብ እንችላለን። እረ ከዚያም አልፎ ስለ ጣምያለው የግድያ ሙከራና በግድያው ሙከራ ስለነበረው ሚና በኩራት ያወራላቸው የላብ አደር መሪዎች ዛሬም አሉ።

"የኢትዮጵያ ላብ አደሮች በ 1968 ዓ/ም ሜይ ደይ አንግበው በተነሱት ሕዝባዊ ጥያቄ ዳፋ ደርግ በመትረየስ አጨዳቸው" ብሎ ከዚህ ቀደም ያወጣው መግለጫ በእጃችን የሚገኝ ሰዎች ዛሬ ደግሞ "ኢሕአፓ በ 1968 ሜይ ዴይ ሰራተኛውን በማስመታት ከሰራተኞች ሞት ስለደርግ ጨካኝነት ማስረጃ ለማግኘት" የፈጸመው መሰሪ ተግባር አድርጎ ጽፎ ሲያስነብበን አቶ ዳዊ ታሪክን በታሪክነቱ ሳይሆን በየወቅቱ እንደ ሚለዋወጠው የፖለቲካ ትኩሳቱ ያለ ይሉኝታ እየቃኘ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት እንደሚጠቀምበት ነው የተረዳነው።

ትላንት በላብ አደሩ ስም ከኔዘርላንድ ሰራተኛ ማሕበር ባገኘው ገንዘብ የአውሮፕላን እና የሆቴል ወጪአቸውን ከፍሎ በክብር የጋበዛቸውን የኢሕአፓውን መስራች አቶ ክፍሉ ታደሰን በአዲሱ አቅዋሙ ኢሕአፓ አስርጋ በሰራተኛው መሃል ያስገባችው የሽብሩ ዋና ሞተር አድርጎ ሲከሳቸው ስናይ ለመሆኑ አቶ ዳዊ አቅዋም ብቻ ሳይሆን ሕሊና የሚባል ነገር ተፈጥሮታል ወይ ብለን መጠየቅ እንገደዳለን።

አቶ ዳዊ በድርሰቱ ማጠቃለያ በሚያስደነግጥ እና በሚያስገርም ድፍረት የኢሰማኮ ጠቅላይ ምክር ቤት በወያኔነታቸው የሰራተኛውን ጥቅም ለገዥዎች ሸጠዋል በማለት ላገዳቸውና ውክልናቸውን ለሰረዘባቸው ታዋቂ የወያኔ ካድሬዎች ለአቶ ታደለ መብራቱ እና ለአቶ አብርሃም ተወልደ የድረሱልኝ ጥሪ አቅርቦላቸዋል። ገና በትግሉ መጀመሪያ ላይ የሰራተኛውን ወገን ከድቶ በቴሌቭዥን በመቅረብ ወያኔን ይቅርታ የጠየቀው ሰለሞን ወንዳየን ጭምር ድረስልኝ ተብሎዋል ። የተሰደዱ የማሕበር መሪዎች ከጎኔ ናቸው ለማለትም እስከዛሬ የት ወደቃችሁ ላላላቸው ስደተኛ የማሕበር መሪዎች የድረሱልኝ ጥሪ አቅርቦአል። አቶ ዳዊ ለስላሳ ተቃዋምሚ ድርጅት ፈብርኮ ወይም ያሉትን አለሳልሶ እና አጅቦ ወደ ሃገር ቤት ለመግባትና ከወያኔ ጋር ለመጎናበስ ውስጥ ውስጡን እየሰራ ነው የሚል ጭምጭምታ የሰማን ቢሆንም አቶ ዳዊ እራሱ የጭምጭምምታውን እውነተኛነት እንዲህ በግልጽ እና በድረ ገጽ ጭምር አውጥቶ ያስነብበናል ብለን ገምተን ግን አናውቅም።

አቶ ዳዊ ኢብራሂም ድረስልኝ ብሎ በግምባር ቀደም የጠራው አቶ ታደለ መብራቱ ወያኔ ሃገራችንን ተቆጣጥሮ የሽግግር መንግስት ሲያውጅ ለወንበር መሙያ እና ማድመቂያ በሰራተኛው ስም ካስቀመጠቻው ሶስት ግለሰቦች አንዱ ሲሆን ኮንፌዴሬሽኑ እንደተቋዋቋዋመ በጠቅላይ ም/ቤቱ ውሳኔ መሰረት ውክልናው ተሸሮ ወደ መደበኛ ስራው እንዲመለስ ሲጠየቅ ወያኔን ተመክቶ አሻፈረኝ ብሎና የሰራተኛውን ውሳኔ ረግጦ እስከ መጨረሻው ያለ ሰራተኛው ውክልና በሰራተኛው ስም በሽግግር መንግስት ውስጥ ወያኔን በቅንነትና በታማኝነት ሲያገለግል ቆይቶአል። የሽግግር መንግስት ሲያበቃለትም የሰራተኛ ተወካይ የሚለው ፌዝ ስላበቃለት ታደለ መብራቱም ላሳየው ታማኝነት ወደ ስዊትዘርላንድ ተልኮ የወያኔን ጥቅም ለማስጠበቅ በግልጽ እና በአደባባይ የወያኔ ደጋፊነቱን አውጆ የኖረ ነው። በስዊትዘርላንድ ቆይታው ወቅት ተቃዋሚዎች በሚያዘጋጁአቸው ሰልፎች ላይ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች እንዳይገኙ እቤታቸው ድረስ እየሄደ ሲያስፈራራ የኖረ ፤ ወያኔ በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን ለማፈን በዘረጋው የዳያስፖራ መዋቅር ውስጥ ታቅፎም ኢትዮጵያውያንን በቤት እና በመሬት በመደለል ለወያኔ እንዲያጎበድዱ ሲደልል የኖረ፤ አሁን በቅርቡ ደግሞ ተልኮውን ጨርሶ ወይም ለሌላ ተልኮ ታጭቶ ጉዋዝ ጉዝጉውዙን ጠቅልሎ ሃገር ቤት የተመለሰ ዝነኛ የወያኔ ካድሬ ነው።

አቶ ዳዊ ከዚህ የወያኔ ካድሬ ጋር ባለው የውስጥ ግንኙነትም ይህ የሰራተኛውን ትግል ከወያኔ ጋር ሆኖ ሲወጋ የኖረ ግለሰብ ወደ ስዊትዘርላንድ ሲመጣ "ለሰራታኛው ሲታገል በወያኔ መንግስት ተዋከቦ የተሰደደ ስለሆነ የስደት መብት ይሰጠው" ሲል የኢትዮጵያ ሰራተኞች ማሕበርን ማሕተም ተጠቅሞ ለስዊትዘርላንድ መንግስት የሀሰት የምስክር ወረቀት ሰጥቶዋል።

አቶ ዳዊ በድርሰቱ ውስጥ የድረስልኝ ጥሪ ያቀረበለት ሁለተኛው ጉዋዱ አቶ አብረሃም ተወልደ ደግሞ ኢሰማኮ ሰራተኛውን በገፍ ያፈናቀለውን ስትራክቸራል አድጀስትመንት ፕሮግራም በመቃወም መግለጫ ሲያውጣና ወያኔ በምላሹ ቁጣውን ሲገልጽ የኮንፌዴሬሽኑን መግለጫ በመቃወም እና የወያኔን እርምጃ በመደገፍ መግለጫ አውጥቶ የመጀመሪያውን የክህደት በር የከፈተ ግለሰብ ሲሆን ፤ ኮንፌዴሬሽኑን በውስጥ ለማመስና ለመበተን በደም ተሳስሮ ይሰራ የነበረው የወያኔ ሻእቢያ ጥምር ጸረ ላብ አደር እንቅስቃሴ ሞተር ከነበሩት ካድሬዎች አንዱ ነው። ወያኔ ኮንፌዴሬሽኑን ለማፍረስ ባካሄደው ጦርነትም በግንባር ቀደም ተሰልፎ ሰራተኛውን የወጋ ሲሆን ኮንፌዴሬሽኑም በፈጸመው ክሕደት ከጠቅላይ ምክር ቤቱ ያባረረው ግለሰብ ነው።

እንግዲህ የአቶ ዳዊ የትግል አጋሮች እነዚህ ናቸው። ከነዚህ ጎን ተሰልፎ ነው በኢሰማኮ ትግል ውስጥ ላንዲት ሰኮንድ እንኩዋን ግንባራቸውን ሳያጥፉ እስከ መጨረሻው በቆራጥነት የተዋደቁትን የሰራተኛ መሪዎች የሚያወግዘው። ይህን የመጨረሻ አይን ያወጣ ክሕደት እኛ የኢትዮጵያ ሰራተኛ ማሕበራት መሪዎችም ሆንን መላው ሰራተኛ ሕዝብ እንዲሁም ታሪክ ከቶውኑ አይይረሱትም።

አቶ ዳዊ በዝነኛው ጥሪው ውስጥ ከዚህ ቀደም በዶ/ር ታዬ ወ/ሰማያት አማላጅነት ሥብሰባ ለመጥራትና የፈጠራቸውን ችግሮች ለመፍታት ተስማምቶ በነበረብት ወቅት በስብሰባው እንዲገኙ ይጠሩ ብለን ካቀረብናቸው ሰዎች ዋስጥ እከሌ ኦነግ ስለሆነ እንዳይጠራ እከሌ ትምክሕት አለበት ወዘተ እያለ እንዳይጠሩ የገዳቸውን ሰዎች ስም ጭምር አስገብቶአል። አዲስ ሊሳፈርበት ላሰበው ባቡር ባለቤቶች እጅ መንሻ መሆኑ ይሆን?

ከሁሉ የሚገርመው ግን አቶ ዳዊ ከሁለቱ ካድሬዎች በስተቀር ስማቸውን የጠራቸውን ሰዎች አድራሻ እንኩዋን አያውቅም ገና አሁን እኛ እንሰባሰብ ስንል ነው ከዘጠኝ ዓመት እንቅልፉ በድንጋጤ ባኖ አድራሻችሁን ላኩልኝ ሃሳባችሁንም ጨምሩልኝ የሚላቸው።

አቶ ዳዊ እነዚህ ሰዎች ለሰራተኛው ትግል ጠቀሜታ አላቸው ብሎ ካሰበ እስከ ዛሬ በምስኪኑ ሰራተኛ ስም ባገኘው ባካፋ የሚዛቅ ዶላር ሽሪኮቹንና እና ግብረ በላዎቹን በአውሮፕላን ከየአገሩ አስመጥቶ ፤ በሆቴል አስቀምጦ ፤ በውሎ አበል ሲያንበሸብሽ እና ሲያቀማጥል ምነው እነዚህን ዛሬ ስማቸውን ከረፈደ የጠራቸውን ሰዎች አላስታወሳቸውም?

አቶ ዳዊ ዛሬ አንተ ድረሱልኝ ብለህ ከጠራሃቸው ሰዎች መሃከል እነ ምትኩ ብርሃኑ ፤ እነ ጌታቸው መንግስቱ ፤ እነ ማሞ ባሳዝን ወዘተ እባክህ ስብሰባ ጥራና ስለሰራተኛው ችግር እንነጋገር እያሉ በፔቲሽን ጭምር ጥያቄ ሲያቀርቡልህ በስድብ እንደወረድክባቸው ረስተህ ነው ዛሬ አይንህን በጨው ታጥበህ እንደ ወዳጅ ድረሱልኝ የምትላቸው?

ዘጠኝ ዓመታት በሙሉ ተሰባስቦ ለመስራት አንዲትም ጥሪ ሳያደርግ ጊዜአችንን በከንቱ ያቃጠለብን አቶ ዳዊ ፤ ከዚህ ቀደም ስብሰባ ይጠራ ብለን ያቀረብናቸውን ፔቲሽኖችና ተማጽኖዎች በስድብ እና በዘለፋ ሲያንጉውጥጥ የነበረው አቶ ዳዊ ዛሬ ምን ተገኝቶ ነው የረሳችውን ስደተኞችና የወያኔ ጉዋዶቹን መጠራራት የጀመረው? ያለፈውን እኩይ ተግባሮችህን እና አሳፋሪ የስነ ምግባር ጉድለቶችህን ለታሪክ እና ለፍርድ ቀን አስቀምጠው ለዛሬው ግን እንሰባሰብ እና እንመካከር ብለው የመጨረሻ ዕድልና ጥሪ ካቀረቡልህ ሰዎች ጋር ከመምካከር ይልቅ ይሕንኑ ቅን እና ግልጽ ጥረት ለማደናቀፍ መሩዋሩውጥስ ማን የሰጠህ የቤት ስራ ነው?

ለመሆኑ አቶ ዳዊ ጥሪ ካቀረብክላቸው ሰዎች መሃል ስማቸው የሚገኝ ሃቀኛ የማሕበር መሪዎች ስማቸውና ታሪካቸው ከነ ታደለ መብራቱ ከነ አብረሃም ተወልደ እና ከነ ሰለሞን ወንዳየን ተርታ አብሮ ተጽፎ ሲያዩ እንዴት ይነዳቸው እንዴት ይገርማቸው ይሆን?

አቶ ዳዊ ከሱ ቀድመው የተሰደዱትን የማሕበር መሪዎች ወረቀት ሲንኮሻኮሽ ፈረጠጡ እያለ ወያኔ ወረቀት ከማንኮሻኮሽ ውጭ ማንንም እንደማይገል እና እንደማያስር ሊመሰክር ቢቃጣውም እሱ የመሰከረለት ወያኔ እነ አሰፋ ማሩን በጠራራ ጸሃይ እየገደለና እነ ዶ/ር ታዬን በፈጠራ ወንጀል 15 ዓመት እያከናነበ ለሲቭል ማሕበረሰቡ የሚቆጥበው ጥይትና ገመድ እንደሌለው አስመስክሮአል።

በአስገዳኝ ሁኔታ ተሰድጄ ወጣሁ ያለን አቶ ዳዊ በውጭ ትግሉን ለማስቀጠል ይሆናል የተሰደደው ብለን የገመትነውንም ወገኖች ውጭ ከወጣ በሁዋላ ባሳየው አፍራሽና እና በታኝ እንዳውም ወያኔአዊ ቅኝት ያለው እንቅስቃሴ ግምታችን ስሕተት መሆኑን አረጋግጦልናል።

ዝርዝሩም እነሆ

አቶ ዳዊ ከሃገር እንደወጣ ቀጣይ የትግል ስልት እና አቅጣጫ ላይ ውይይት ለማድረግ ቀድመን የተሰደድነውን የአመራር አባላት እሱ ያለበት ሃገር ድረስ በመምጣት ስብሰባ አድርገን አቅጣጫ ቢነደፍም የነደፍነው አቅጣጫ ዳዊ በልቡ ይዞት ለነበረው የግል ፓለቲካ ፓርቲ ምስረታ አጀንዳ የማያመች እና በሲቭክ እንቅስቃሴ ላይ ብቻ ያተኮረ በመሆኑ ውሳኔውን የውሃ ሽታ አድርጎ አስቀርቶታል። ታሪካዊዉ  ቃለ ጉባኤ ግን በ እጃችን ስለሚገኝ ዛሬም  ማቅረብ እንችላለን።

ከስደት በሁዋላ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1998 ዓ ም ጀኔቫ ሲመጣም እንደገና የ እንሰባሰብ ጥያቄ ቀርቦለት ከንግዲህ የፖለቲካ ፓርቲ እንጂ የሰራተኛ ማሕበር ትግል ዋጋ እንደሌለው ለፓርቲ ምስረታውም በቂ የሰው ሃይልና የገንዘብ ምንጭ እንዳገኘ ነግሮን እንድንተባበረው ጥሪ አቅርቦልን ነበር። በበኩላችን የኢትዮጵያ ሰራተኞችን አደራ በዛ ቀውጢ ወቅት ሜዳ ላይ በትነን ወደ ፓርቲ ምስረታና የስልጣን ሽሚያ መሮጡ ክህደት ስለሆነ በዚህ ክህደት እንደማንሳተፍ እሱም በዚያ አቅጣጫ ከተጉዋዘ እንደምናጋልጠው ነግረነዋል። የኛና የአቶ ዳዊ ልዩነት ግልጽ  የሆነዉም ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው። ይህንን ደግሞ ከሃገር ቤት ለስብሰባ በመጡት ወንድሞቻችን ፊት ከዓመታት በፊት የተናገርነው ስለሆነ ዛሬ ሁሉም ሊመሰክሩት የሚችሉት ነው።

በስደት የምንገኝ የማህበራት መሪዎች ከነገ ዛሬ ስብሰባ ተጠርቶ ትግሉን አቅጣጫ ለማስያዝ እንመካከራለን ብለን ብንጠብቅም ዳዊ ድምጹን አጥፍቶ በመደበቁ እና ሁኔታዉም በእጅጉ ስላሳሰበን በወቅቱ በውጭ እንገኝ ከነበርነው አስራ አንድ ስደተኛ የማሕበር መሪዎች ስምንታችን የተስማማንበት እና የፈረምንበት ስብሰባ ጥራንና እና ለኢትዮጵያ ሰራተኞች እንድረስላቸው ፤ ለአሰፋ ማሩ ቤተሰቦች እንድረስላቸው፤ ለ እስረኛው ዶር ታዬ እንድረስላቸው ስንል የተማጽኖ ደብዳቤ ልከንለት በምላሹ እጅግ አሳፋሪ የሆነና በተራ ዘለፋ ስድብ እና በዛቻ የተሞላ ደብዳቤ ልኮናል። የተማጽኖ ፔቲሽናችንን እና አቶ ዳዊ የሰጠንን አስጸያፊ የዘለፋ ምላሽ ወደፊት በአማርኛ ተርጉመን ለሕዝብ ንባብ እናበቃቸዋለን። [ለአሁኑ ግን የቴቲሽናችንን እንግሊዝኛ ኮፒ  ከዚህ ጽሑፍ ጋር አባሪ አድርገን ስለላክን  የዚህ ድረ ገጽ ባለቤት ከጽሁፋችን ጋር እንዲያትሙልን እንጠይቃለን]

በኢትዮጵያ ሰራተኞች ስም ከኔዘርላንድ ሰራተኛ ማሕበር በተገኘ ገንዘብ አቶ ዳዊ በጠራው የመጀመርያ ስብሰባ ዛሬ የኢሕአፓ ሰርጎ ገብ እያለ የሚዘልፋቸውን የኢሕአፓውን አቶ ክፍሉ ታደሰን ጨምሮ ለፓርቲ ምስረታዬ ይረዱኛል የፖለቲካ ሽሪክ ይሆኑኛል ብሎ ያሰባቸውን እና ያሰባሰባቸውን ቁጥራቸው የበዛ ሰዎች ሙሉ ወጪአቸውን ሸፍኖ በመጋበዝ የኢትዮጵያን ፖለቲካ ሲያስተነትን ስለ ኮንፌዴሬሽኑ ያለፈ ትግል ግምገማና የወደፊት አቅጣጫ እንዲሁም የማሕበር መሪ በመሆናቸውና የኮንፌዴሬሽኑን አቁዋም በመደገፋቸው ከስራ ተባረው ከነ ቤተሰቦቻቸው በረሃብ በመገረፍ ላይ ስለነበሩት የስራ ባልደረቦቻችን ሕይወትና እንዴትም ልንረዳቸው እንደምንችል ውይይት ሳይካሄድ ስብሰባው ተበትኖአል። በወቅቱ የአቶ ዳዊ አካሄድ የፖለቲካ ፓርቲ ምስረታ ሽር ጉድ እንደሆነ ገብቶን ከንግዲህ ቀጣዩ የትግል አቅጣጫ ተበታትነው በወያኔ  በትር እየተመቱ ያሉትን ሲቭክ ማህበራት ኢሰመጉን ኢመማን የጋዜኞች ማሕበርን እና ሌሎችንም ነጻ ማሕበራት ወደ ጋራ የትብብር እና የትግል አጋርነት መድረክ በመምጣት ወያኔን መቁዋቁዋም መሆን ይገባዋል የሚል ጽሑፍ አዘጋጅተን ለማቅረብ እድል ብንጠይቅም የፓርቲ ምስረታውን ሽር ጉድ መስመር የሚያስት ጽሑፍ በመሆኑ እድል በመነፈጋችን  በግል ወጫችን ጽሑፉን አባዝተን ለተሳታፊዎች አድለናል። በዚህ ስብሰባም ስለ ኮንፌዴሬሽናችን ችግር እና ስለ ትግላችን ቀጣይ አቅጣጫ ምንም ሳይባል ስብሰባው በመበተኑና ከስራ ተባረው በከፍተኛ ችግር ላይ ስለነበሩት ወንድሞቻችንንም ምንም ምክክር እና እርዳታ ባለመደረጉ ያዘንን እና የተቆጨን የማህበር መሪዎች አቶ ዳዊ መድረክ የነፈገውን የኢትዮጵያ ሰራተኛ ማሕበር ቀጣይ ትግል እና ከስራ ተባረው የተቸገሩ  የማሕበር መሪዎችን ጉዳይ  እዚህ ድረስ መጥተን ሳንወያይ አንበተንም ብለን አቅዋም በመውሰድ በሆቴል ቤት ለአንዳችን በተያዘ  ክፍል ውስጥ ስብሰባ ጠርተን አቶ ዳዊንም በአማላጅ አስጠርተን በሆቴል ቤት ክፍል አቶ ዳዊ የአዳራሽ ክብር የነፈገውን የማሕበራችን ኢሰማኮን ጉዳይ ለመወያየት ተገደናል። በዚህ ስብሰባ ትግሉን ለመበተን አቶ ዳዊ የፈጸማቸው ክሕደቶች እና በኛ በኩል ለመሰባሰብ የተደረጉ ጥረቶች እንዲሁም አቶ ዳዊ የፈጸማቸው አስነዋሪ ተግባራት፤ ከአዲስ አበባ በመጡት የማሕበር መሪዎች ፊት አቶ ዳዊ ጭምር ባለበት በዝርዝር ቀርበዋል። በወቅቱ በስብሰባው የተገኘን ስደተኛ የሰራተኛ መሪዎች ከስራ ተባረው በችግር ላይ ያሉ ሰራተኞችንና የሰራተኛ ማሕበር መሪዎችን በቁዋሚነት ለመርዳት ወርሃዊ መዋጮ ለማድረግ አካውንት እንዲከፈትልን፤ ወደ ውጭ መሰደድ የሚገደዱ ካሉም አስፈላጊውን እገዛ ለማድረግ እንድንችል አድራሻቸው እንዲሰጠን ወይም አድራሻችን እንዲሰጣቸው፤ አባቱ ሞቶበት በዩኒቨርስቲ ትምሕርቱን ይከታተል የነበረ አንድ የሙት ጉዋደኛችንንም  ልጅ በግልና በጋራ ለመርዳት አድራሻው እንዲሰጠን ወይም አድራሻችን እንዲሰጠው ወዘተ ጠይቀን ሁሉንም ሃሳቦች አቶ ዳዊ አልቀበል ብሎ በብጥበጣ በማስቸገሩ ያለምንም ውሳኔ ቀርተዋል። የኢሰማኮን ቀጣይ የትግል አቅጣጫም ለመንደፍ ያደረግነው ጥረት አቶ ዳዊ ሆን ብሎ ስብሰባው እንዳይቀጥል እና በጸብ እንድንለያይ በተሰብሳቢዎች ላይ ይወረውራዋቸው በነበሩ ጸያፍ ቃላት በተፈጠረው ሁካታ ሳይሳካልን ቀርቱአል። ከዚያም በላይ ደግሞ ዳዊ በአንዲት ሴት ላይ ፈጽሞት በነበረው ጸያፍ እና ነውር ወንጀል ላይ በተከፈተው አጀንዳ አብዛኛው ተሰብሳቢ በመሸማቀቁና በሀፍረት እና በንዴት ስሜት ውስጥ በመግባቱ ሁኔታው እንኩዋን ቀጣይ የትግል አቅጣጫን ከንግዲህ የአቶ ዳዊን አይን ማየትም የማያስመኝ ሆኖ ተለያይተናል። በበኩላችን ግን ለውሎ አበል የተሰጠንን ገንዘብ ከስራ ተባረው ለተቸገሩ የማሕበር መሪዎች ከአዲስ አበባ ለስብሰባው ተጋብዘው መጥተው በነበሩ የማሕበር መሪ እጅ ልከናል።

ወረቀት ሲንኮሻኮሽ ፈረጠጡ የተባልነው የአመራር አባላት እግራችን ለስደት ከተዳረገበት ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ ሰራተኞች የሰጡንን አደራ ከግብ ለማድረስ ከፍተኛ ጥረት አድርገናል። አረመኔአዊውን የወያኔ አገዛዝ ግንባራችንን ሳናጥፍ ታግለነዋል። ከሌሎች በውጭ

ሃገር ከሚገኙ ኢቲዮጵያውያን ጎን ቆመን ከሰላማዊ ሰልፍ እስከ ሕዝባዊ ስብሰባ ፤ ከቁሳቁስ ማሰባሰብ እስከ ምራባውያን አገሮችና ኤምባሲዎች በር ማንኩዋኩዋት ፤ ከከተማ ከተማ ካገር አገር ተጉዋጉዘን ከወገኖቻችን ጎን ቆመናል ። የኢትዮጵያን ሕዝብ ሰቆቃ አስተጋብተናል። ከውጭ ሆኖ ሕዝባችንን በማስተማርና በመቀስቀስ ከፍተኛ ሚና ለተጫወተው የትንሳኤ ሬድዮ ገንዘብ አሰባስበን ልከናል። ቅድመ ምርጫ 97 እንቅስቃሴ ውስጥ ተካፍለናል። የኢትዮጵያ ላብ አደር ድምጹን ለኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች በመስጠት ወያኔን እንዲቀጣው በጋዜጣ ጭምር ጥሪ አቅርበናል። ድሕረ ምርጫም በምርጫ 97 መዘዝ በአጋዚ ጦር በግፍ ለተጨፈጨፉት ኢትዮጵያውያን እርዳታ አሰባስበን ልከናል። የታሰሩ የሕዝብ መሪዎች ጋዜጠኞች ንጹሃን ዜጎች ባጠቃላይም የሕሊና እና የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ ጮኻናል። ከአንድነት ሃይሎች ጎን ቆመን አቅማችን የፈቀደዉን ሁሉ አድርገናል። በያለንበት አካባቢ የሐገራችንን እና ሕዝባችንን አጀንዳ ከፍ አድርገን ስንታገል ቆይተናል። በየመድረኩ የኢትዮጵያን ጠላቶች አጋልጠናል። ለሐገራችን ለኢትዮጵያ እና ለሕዝቡዋ መብት መከበር ያለማቁዋረጥ ታግለናል።

የኢትዮጵያ ልጆች ከወያኔ ጋር ጉሮሮ ለጉሮሮ ተናንቀው ወሳኝ ፍልሚያ ባካሄዱባቸውና ታላቅ ድል በተቀዳጁባቸው ቅርብ ዓመታት አቶ ዳዊ ማን ጉያ ውስጥ እንደነበረ ድፍን የአምስተርዳም ነዋሪ የሚታውቀው የአደባብይ ምስጢር ነው። በማሕበራዊ ጉዳይ ነው ግንኙነታችን እያለ በቅርቡ ሊሸፋፍነው እንደሞከረው ሳይሆን እነዚህን ወያኔአዊ ጉዋዶቹን በኢትዮጵያ ላብ አደሮች ስም በተለመነ ገንዘብ አቶ ዳዊ አምስተርዳም ላይ ባዘጋጀውና ሃቀኛ የሰራተኛ ማሕበር መሪዎችን በራሱ የግል ውሳኔ ባገደበት ስብሰባ ላይ በክብር ጋብዞአቸው እንደነበረ ከነ ስማቸው ሊስቱን ማቅረብ እንችላለን። በመሆኑም ግንኙነታቸው አብረው የተደራጁበት እና አብረው የሚሰሩበት እንጂ ማሕበራዊ አይደለም። አቶ ዳዊ በነዚህ ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን በተፈተኑባቸው ወሳኝ ዓመታት በአንድም ቦታ ላይ ከኢትዮጵያውያን ጎን ቆሞ ታይቶ አያውቅም። አሁን ዶፉ ካባራ ጎርፉ ካለፈ በሁዋላ ከተደበቀበት በደላላ ተጠርቶ መጥቶ ያለኔ ታጋይ ላሳር እያለን ነው።

በማሕበራችን ላይ እየደረሰ የነበረውን ግፍ እና እመቃ ለዓለም አቀፍ አጋር ማሕበራትና ለ I L O አይ ኤል ኦ በማሳወቅ እና ያላሰለሰ ክትትልም በማድረግ የኢሰማኮ ጉዳይ ከፍተኛ ትኩረት እንዲያገኝ አድርገናል። በዓመታዊው የ I L O አይ ኤል ኦ ኮንፈረንስ ላይ በተከታታይ አመታት የኢትዮጵያ ሰራተኞች ድምጽ በመሆን በሙሉ ተሳታፊነት ተካፍለን የወያኔ ተላላኪ የሆኑትን ከሃዲዎችና የሃሰት ዘገባዎቻቸውን በማጋለጥ አስወግዘናቸዋል።

በአንጻሩ አቶ ዳዊ ከተሰደደ በሁዋላ እነዚህን ፋይሎች በከፍተኛ ክትትል ሕይወት ሰጥተዋቸው ያቆዩአቸዉን ሰዎች በስድብና አሉባልታ አላሰራ ብሎ፤ ከአለም አቀፍ አጋር ማሕበራት ጋር አላስፈላጊ አተካሮ በመግባትና በመጨረሻም ከናካቴው ጥሎ በመጥፋት የኢትዮጵያ ሰራተኞች አቤቱታዎችና ፋይሎቹ ተከታታይ እና አስታዋሽ አጥተው ተራ በተራ ተዘግተዋል። አቶ ዳዊ ግን ዓለም አቀፍ ማሕበራትን አሳምኖ በአንድም የ I L O አይ ኤል ኦ ስብሰባ ላይ ገብቶ ለመሳተፍ ዕድሉን ሳያገኝ ዛሬ የኢሕ አፓ ሰርጎ ገብ ያላቸው አቶ ክፍሉ ታደሰ በሚያሳትሙት ዜጋ መጽሔትና ጦቢያ መጽሔቶች ላይ በሰጣቸው ቃለ ምልልሶች ከፍተኛ ትግል በ አይ ኤል ኦ እያካሄደ እንደሆነ ሱዋሽ በማተት የሐሰት ዘገባ ሲያቀርብ ኖሮዋል። በወቅቱ እነዚህን መሰረተ ቢስ የሃሰት የክንውን ሪፖርቶች ማተም አቁሞ እውነተኛ ስራ እንዲሰራ በውጭ የምንገኝ ስደተኛ የማሕበር መሪዎች በፔቲሽን ጭምር ተፈራርመን ጠይቀነዋል ።

ስብሰባ ይጠራና ትግሉን አቅጣጫ እንስጠው፤ ግልጽነት እና ተጠያቂነት ያለበት የጋራ አሰራር እና አመራር እንፍጠር፤ በማለት በተከታታይ ለቀረበለት ፔትሽን አሳፋሪ የስድብ ናዳ እያወረደ ያለምንም ሃፍረት ዜጋ መጽሔት ላይ እና ጦቢያ መጽሔት ላይ በሰጣቸው ቃለ መጠይቆች የተሰደዱ የሰራተኛ መሪዎችን እያሰባሰብኩ ትግሉን እያስቀጠልኩ ነው ሲል ዓይኑን በጨው አጥቦ የሐሰት ዘገባ ሲይያቀርብ ኖሮዋል።

ለሁለተኛ ጊዜ በኢትዮጵያ ሰራተኞች ስም ከኔዘርላንድ ሰራተኛ ማህበር በተገኘ ከፍተኛ ገንዘብ በተጠራው ስብሰባም ለዳዊ አምባ ገነናዊና መረን አካሔድ ያላጎበደዱትን ሃቀኛ የማሕበር መሪዎች ከስብሰባ በማገድ በተካሄድው ብዙ ፖለቲከኞች የተጋበዙበት የዳዊ ፓርቲ ምስረታ ሁለተኛ ዙር ሽር ጉድ አሁንም ለሁለተኛ ጊዜ በስሙ ዶላር የሚታፈስበት የምስኪኑን ሰራተኛ ጉዳይ ከአፍ ማሙዋሻ ያለፈ ትኩረት ሳይሰጠው ተጠናቀቀ። እንደተለመደው የፓርቲ ምስረታ ሽርጉዱን ያደናቅፉብኛል ብሎ የፈራቸውን ሃቀኛ የማሕበር መሪዎች ወደ ኔዘርላንድ እንዳይመጡ የግብዣ ደብዳቤና ትኬት ሳይልክ እንዲገኙ ጋብዣቸዋለሁ የሚል የሃሰት ወሬ ሲያናፍስ የፈራዋቸው ሃቀኛ የማህበር መሪዎች በግል ወጪያቸው ኔዘርላንድ ድረስ በመገኘት በስብሰባው እንዳይገኙ በአቶ ዳዊ የግል ዉሳኔ መታገዳቸውን ለተስብሳቢዎች ፤ ለኔዘርላንድ ሰራተኛ ማሕበር እና በኔዘርላንድ ለሚገኙ ስደተኛ የነጻ ጋዜጣ ቤተሰቦች አሳውቀዋል። በዚህ አጋጣሚ በኔዘርላንድ የሚገኙ የነጻው ፕሬስ አባላት በስደት የምንገኝ የሰራተኛ ማሕበር መሪዎች ያደረግነውን ጥረት እና በአቶ ዳዊ እጅ የደረሰብንን እንግልት ለኢትዮጵያ ሰራተኛ እና ሕዝብ በማቅረብ አቶ ዳዊ የጀመረውን ሃቅን በግፍ አካፋ የመቅበር እኩይ ዘመቻ እንዲያጋልጡ ሕዝብ የማወቅ መብት ስላለው በኢትይጵያ ሕዝብ እና ሰራተኞች ስም እንማጸናቸዋለን።

በመጨረሻም ይህን የመጀመሪያ ለአቶ ዳዊ ድርሰት ያቀረብነውን ምላሽ የምናጠቃልለው አቶ ዳዊ የፈጸማቸውን አውራ የስነ ምግባር ጉድለቶች እና ወንጀሎች በአጭሩ በማቅረብ ነው።

1 - በኢትዮጵያ ሰራተኛ ማሕበራት ኮንፌዴሬሽን (ኢሰማኮ) ማሕተም በ ኢሰማኮ ትግል ውስጥ ተሳትፋ ለማታውቅ አንዲት ሴት የኢሰማኮ የሴቶች ዴስክ ሃላፊ ነበረች መንግስት በዚያ ምክንያት ሲያሳድዳት ነው ሃገር ለቃ የውጣችው በማለት የሃሰት ማስረጃ ከመስጠቱም በላይ ለዚህ ውለታው የወሲብ ጉቦ በመጠየቁ በተነሳው ውዝግብ በሴቲቱ ላይ ድብደባ መፈጸሙ ጭምር ከአዲስ አበባ በመጡ የማሕበር መሪዎች ፊት በአጀንዳ መነሳቱና መጋለጡ። አቶ ዳዊ ሴቲቱን የሃሰት ታሪክ ለማስጠናት በራሱ የእጅ ጽሁፍ ያዘጋጀው ባለ ብዙ ገጽ ሰነድ በጃችን ስላለ ወደፊት በድረ ገጽ እናወጣዋለን።

2 - በኢትዮጵያ ሰራተኛ ማሕበራት ኮንፌዴሬሽን (ኢሰማኮ) ማሕተም አቶ ታደለ መብራሕቱ ለተባለ በኢሰማኮ የተወገዘና የታወቀ የወያኔ ባለሙዋል ከ ኢሰማኮ ጎን ቆሞ በመታገሉ ወያኔ ያጉላልው ኢና ያሰደደው አስመስሎ የሃሰት ማስረጃ ጽፎ ሰጥቶታል (ደብዳቤው በእጃችን ይገኛል)

3 - በሰራተኛው ስም ላለፉት 12 ዓመታት ከ ዓለም አቀፍ አጋር ማሕበራት ሲጎርፍ የኖረውን ገንዘብ ያለምንም ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለ ምንም የሂሳብ ሪፖርት በግሉ እንዳሻው ተጠቅሞበታል።

4 - የተሰደዱ የማሕበር መሪዎችን አሰባስባለሁ በማለት ከኔዘርላንድ ሰራተኛ ማሕበር በሁለት ጊዜ ከመቶ ሺ ዶላር በላይ የሆነ ገንዘብ ያለምንም ተጥያቂነትና ግልጽነት ባሻው አጥፍቶታል።

5 - ከስራ የተፈናቀሉ የማሕበር መሪዎችን በሃገር ውስጥ አቋቋቁማለሁ በማለት ከኔዘርላንድ ሰራተኛ ማሕበር በፕሮጀክት ስም የወሰደውን ገንዘብ በሀገር ውስጥ ምንም ፕሮጀችት ሳይከፍትበትና ማንንም ሳይረዳበት የት እንደገባም ሳይታወቅ በግሉ እንዳሻው አጥፍቶታል።

6 - ከላይ በተራ ቁጥር አንድ ለአንዲት ሴት የጻፈውን የሃሰት የምስክር ወረቀት ሴትዮዋ አቶ ዳዊ ላቀረበላት የወሲብ ጉቦ ጥያቄ አሉታዊ መልስ በመስጠትዋ ሲፋረሱ ያለምንም ህፍረት አሁንም በኢትዮጵያ ሰራተኛ ማሕበራት ኮንፌዴሬሽን (ኢሰማኮ) ማሕተም ሴቲቱ አሳስታኝ ተሳስቼ ነው ደብዳቤ የጻፍኩላት በማለት የመጀመሪያውን ደብዳቤ መሻሪያ ደብዳቤ በመጻፍ እራሱን አጋልጦአል።

7 - የኔዘርላንድ ሰራተኛ ማሕበር ለኮንፌዴሬሽኑ ስራ ማስኬጃ ሰጥቶት የነበረው ገንዝብ አያያዝና የአቶ ዳዊም የስነ ምግባር ጉድለቶችንም በሚመለከት ከላይ እንደገለጽነው የኢሰማኮን ማሕተም ተጠቅሞ የጻፋቸው የሐሰት ማስረጃዎች በኔዘርላንድ የስደተኛ ቢሮ አማካይነት ስለደረሳቸው ፤ እነዚህ ተደማምረው ሁኔታው አሳሳቢ ደረጃ በመድረሱ የኔዘርላንድ ሰራተኛ ማሕበር ቢሮውን ቀምቶ አባሮታል።

እንግዲህ እነዚህና ሌሎችም ኢዚህ ያላነሳናቸው ጉዳዮች በመድረክና በውይይት ተነስተው እወገዛለሁ ወይም ከመሪነት እታገዳለሁ ከሚል ባዶ ጭንቀት በመነሳት ነው የኢትዮጵያ ሰራተኛ ማሕበር መሪዎች እንዳንገናኝ አቶ ዳዊ ከድሮ ጀምሮ ሲተናነቀን የኖረው።

ዛሬ ለዓመታት አምቀናቸው የኖርናቸውን የአቶ ዳዊ የቅሌት ሬከርዶች አደባባይ ያወጣናቸው አቶ ዳዊን ለማጋለጥ አይደለም። እነዚህን ጉዳዮች ድፍን የአምስተርዳም ኑዋሪ ኢትዮጵያውያን እና የነጻው ፕሬስ ቤተሰቦች ከዓመታት በፊት ጀምሮ ያውቁአቸዋልና አዲስ የሚጋለጥ ሚስጥር የለም። ሆኖም አቶ ዳዊ ሰሞኑን እማያቀው ያለ ይመስል ቁርበት አንጥፉልኝ ማለት ጀምሮአልና የዛሬ አጃቢዎቹን ከኛ ተማሩ ለማለት ነው።

በተጨማሪም አቶ ዳዊ ዛሬ በስድስት ገጽ ጽፎ ያወጣውን ድርሰት በኔዘርላንድ በሚገኘው ድር ኢትዮጵያ በተሰኘ አፍቃሬ ወያኔ ሬድዮ ጣቢያ ላለፉት ሰባት ዓመታት ሲያቀርበው የኖረ በመሆኑ ዛሬ አዲስ የሚጋለጥ ነገር የለም አዲስ ነገር ቢኖር አቶ ዳዊ ሰባት ዓመት ሙሉ በወያኔ ሬዲዮ አቅርቦት ሰሚ ያላገኘለትን ድርሰት ይዞ ወደ ተቃዋሚዎች የፖለቲካ ገበያ ብቅ ያለው ምን ብርቱ ደላላ አይዞህ ቢለው ነው የሚለው መጠይቅ ብቻ ነው።

አቶ ዳዊ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሂደት ባለፉት 35 ዓመታት ከ ኢሕ አፓ ወደ ደርግ ከደርግ በፎረም 84 አድርጎ ወደ ወያኔ ከወያኔ እንደገና ወደ ኢሕአፓ ከኢሕአፓ እንደገና ወደ ወያኔ ሲገላበጥ ኖሩዋል። በሂደቱም አብረውት የተሰለፉትን ጭዳ አድርጎ ነው የተረማመደባቸው። ባሁኑ ወቅትም የተነሳውን የፖለቲካ አቡዋራ ተከልዬ አንዱ ድርጅት ዘው ማለት አያቅተኝም በሚል ስሌት በየመድረኩ ታጋይ ለመምሰል ያዙኝ ልቀቁኝ እያለ ነው። ዛሬ በብዙ መስዋዕትነት ከወደቀበት እየተነሳ እና ከደረሰበት ስብራት እያገገመ ያለውን ጎራ የተለመደውን የአፍ ጉቦ በመስጠት እንድ ዘንዶ ሊጠመጠምበት ሲያደባ ስናይ ከልምዳችን ተማሩ ማለት እና መጮህ እንገደዳለን ። የታወቀና የተመሰከረለት ከሃዲ ለተራና ጊዜአዊ የፖለቲካ ትኩሳት ማስታገሻ ይጠቅመናል በሚል ተሸክመው ወደ ሕዝባዊው መድረክ እምብርት እያስገቡት ያሉት ወገኖች የትሮጃን ሆርስ ሚና እየተጫወቱ ነዉና ተጠንቀቁ ማለት ዳዊን በሚገባ ከምናውቅና ከክሕደቱና ከቅጥፈቱም ከቀመስነው ዜጎች የሚጠበቅ በመሆኑ እባካችሁ በኢትዮጵያ ሕዝብ አንገት ላይ መርዘኛ ዕባብ አትጠምጥሙ እንላለን።

በመጨረሻም በመላው ዓለም ተበትናችሁ ያላችሁ በቀድሞ የኢትዮጵያ ሰራተኞች ማሕበር ትግል ከመሰረታዊ ማሕበር እስከ ኮንፌዴሬሽኑ ድረስ ተሰልፋችሁ ወያኔን የታገላችሁ የሰራተኛ መሪዎች አዲስ በጀመርነውና ገና በውጥን ደረጃ ባለው የመሰባሰብ ጥሪ በመሳተፍ በጋራ ሕገ ማሕበራችንን ነድፈን ድምጽ ለተነፈገው የኢትዮጵያ ሰራተኛ እና ለሕዝባችን ድምጽ እንድንሆነው ኑ አብረን እንቁም፤ ኑ የኢትዮጵያን ሕዝብ የዲሞክራሲ ፤የነጻነት ፤የዕኩልነት፤ የአንድነትና የሰላም ትግል እናግዝ እያልን ጥሪያችንን እናቀርባለን። በዚህ ጥረት ለመሳተፍም በሚከተለው ኢሜል አድራሻ ልታገኙን ትችላላችሁ፡፡ workersvoiceforum@gmail.com

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!

ሰራተኛው መብቱን በትግሉ ያስከብራል!

Hailu OURGESSA
Rue des Crêtes 28
1018 Lausanne
Switzerland
E-mail, ourgessa@yahoo.com

Lausanne March 6, 2001

Mr. Dawi IBRAHIM
C/o FNV
Postbus 8456
1005 AL AMSTERDAM

Dear Brother Dawi

Here with, Please find petitions signed by the participants of the Ethiopian workers struggle for a free independent and democratic trade union in Ethiopia .The signatories are: -

1. Mr.Abera Mengistu Secretary EELPA Trade Union Now residing in Belgium
2. Mr.Ayalew Hundessa EELPA Labor union Now residing in Australia
3. Mr.Essayas Berhanu IFBTTU Secretary Now residing in Austria
4. Mr.Getachew Abera General secretary Am.Be.branch Now residing in Norway
5. Mr.Getachew Mengistu General Secretary of EBIF Now residing in USA
6. Mr.Hailu Ourgessa Ex. President Federation of CTP Now residing in Switzerland
7. Mr.Mamo Basasin Deputy Sec. Federation of CTP Now residing in Norway
8. Mr.Mitiku Berhanu CETU Supreme council member Now residing in USA

We are all asking for a meeting. Nothing else. Just a meeting.

If you can secure a financial or/and technical assistance from our friends in FNV or other friendly unions that would help. But lack of fund should not hinder us from working for the cause we have already paid dearly. So we propose as an alternative that every participant shall bear his expense in case you failed to secure the required assistance.

As you very well know the problematic financial situation that most of us are found in, this proposal will definitely tell you how keen we are to work for the cause.

The Ethiopian workers are hoping that we will do our most to fight for the observance of their right, to keep the struggle alive and keep the torch of hope high. They need our effort to save their family. The massive dismissals have continued to force families' breakdown. As various studies suggested the children of the workers are much in the streets than in schools; begging and peddling. The situation in Ethiopia is worsening day by day. The Ethiopian workers, who have elected us to lead the struggle, are forced in to silence. Those of us who have escaped the cruel repression did understand that we bear the legal and moral responsibility to continue the struggle.

Our friends in prison like Mr Hailemichael Chanea the secretary of CETU's Awasa branch office, Dr. Taye wolde Semayat president of Ethiopian teachers association (ETA), etc...surely need our voice and effort to liberate them from the dungeons of the regime in Ethiopia.

The families of Mr. Assefa Maru and other martyrs of the Ethiopian civic movement need our help in every aspect from their daily bread up to the legal battle to bring the culprits to justice.

There are many more good things that we can do for the civic empowerment if we can reorganize our selves and move in a genuine manner without failing prey to the evil forces that try to paralyze and annihilate this great struggle through blackmail, cheap political manipulation, and creating division.

We have already lost years waiting for your call. Please for the poor worker's and their family's sake, do not make us loose another year in silence.

Being encouraged by the fact that no serious activity is witnessed, and that we are not acting in an organized manner, the stooges in CETU office are in full swing to pose them selves as genuine trade unionists and pledge allegiance and solidarity with the international trade union movement.

This malicious and futile effort by the stooges and their mentors in the palace, if not properly tackled in unison, will, in no uncertain terms, push the genuine movement in to isolation. There fore it is high time to wake up and act before it is to let.

As the aim of this letter is to bring unity and consensus among all Ethiopian trade union leaders in exile, we have reached all of them .All with out exception have agreed to the idea. The petitions that are not included in this letter are believed to have reached you directly.

The signatories to the petition are eager to hear from you very urgently if you are willing to call the much-needed meeting or not. They are eager to hear from you about the struggle from which they have been marginalised for years.

Our effort is to create unity and consensus; accordingly, you are expected to send your answer to all of us without marginalising any trade union leader. As the purpose is not to engage and excel in polemics we expect a genuine answer from you.

Our call is for collective leader ship, accountability and transparency that our struggle lacked for years. Our hope is that you will act wisely and responsibly.

We expect you to heed this genuine call. We hope you won't prefer to continue acting on your private agenda and personal ambitions. We believe you won't keep on marginalising the legally elected representatives of the Ethiopian workers.

If you do; let it be known to you that we will be forced to communicate with our national and international friends; on whom we have a solid trust, to mediate the situation and rescue this great struggle from falling in tatters.

Yours sincerely

HAILU GURGESSA
EX PRESIDENT FEDERATION OF COMMERCE, TECHNIC AND PRINTING INDUSTRY TRADE UNIONS

NB. This is our second call after you refused to answer to our letter (similar to this one) dated February 3, 2001

Brother Dawey:-

It has been three years since you were forced into exile and it has also been three years since we kept hoping that you will reorganize the exiled trade union leaders and members by calling a meeting to discuss about our struggle to build an independent and democratic trade unionism in Ethiopia and to draft the way forward. We have hoped that collective leadership accountability and transparency still have their place in the leadership and firmly believed that the responsibility of keeping alive the struggle is shared by all of us, as we too are elected leaders and members of CETU.

In order to live up to the expectations of the Ethiopian workers who elected us to lead them into the future where democratic trade unionism replaces the shadow trade unions that breath with the lung of the regime in power as has been witnessed during the military regime and in today's Ethiopia too, the struggle needs collective transparent and accountable leadership.

The absence of these three pillars of democratic leadership and the continued marginalization of elected members of CETU has resulted in a one man scenario. While everything is planned and executed by you alone, even without any verbal or written report to the elected leadership during the last three years, you have continued pretending as if there exists collective leadership. You have also kept pretending to the international trade union movement as if you are working in consultation with us while it is you and you alone who is acting as CETU. You have repeatedly stated in your interviews with the mass media that you are reorganizing the worker's family, while you have never made any effort to this effect.

When we examine your performance during the last three years there is much to worry about the credibility of your leadership. Our silence for the last three year was meant not to give advantage to the enemies of democracy and in order not to frustrate those workers who bestowed such a big responsibility on our shoulder and to give you enough time to realize what you are supposed to do and what you actually kept doing.

In the absence of any improvement in your conduct so far we are obliged us such to voice collectively after learning that different individual efforts to convince you to call a meeting to establish a working relationship with us, to answer to our questions, and to listen to our advice has been rejected by you.

So we here by call up on you to return to the civilized culture of democratic trade unionism, to reestablish your credibility through transparent and accountable leadership to call an urgent meeting and to stop disinforming the international trade union movement, the Ethiopian public in general and the Ethiopian workers in particular.
We reaffirm our commitment to keep the struggle alive and vibrant until the ideals of independent and democratic trade unionism is realized in Ethiopia.

| NAME | ADRESS (FAX/PHONE) | RESPONSIBILITY IN THE TRADE UNION | SIGNATURE |
|---|---|---|---|
| MITIKU BERHANU | 703 379 8744 | Council member | Mitiku Berhanu |

5753 HARWICH CT #233
Alexandria VA 22311
USA